# የብሔር ጥያቄና የኢትዮጵያ ኣንድነት

ዶ/ር ገላውዴዎስ ኣርኣያ

ኣሁንም እንደገና የብሔር ጥያቄ በኢትዮጵያ ያገረሸ ይመስላል። ሰሞኑን በኣመሪካ ድምጽ ረድዮ ኣስተናጋጂነት ኣቶ ሌንጮ፡ ኣቶ ገብሩና ዶ/ር ሺመልስ በሰል ባለ መልኩ ስለ ብሔር ጥያቄና ምን መደረግ እንዳለበት በመጠኑም ቢሆን ተንትነው ኣቅርበውታል። ውይይቱ ከሞላጎደል የኢትዮጵያ ታሪክና የፖለቲካ ዝምድናዎችን የምያንጸባርቅ ሆኖ ርትዓዊ ትንታኔም ነበር ማለት ይቻላል። ሆኖም ግን ስለ ኢትዮጵያ ኣንድነት ይኸን ያህል ትኩረት የተሰጠው ኣይመስለኝም። ስለሆነም በዚሁ ጽሑፍ የብሔር ጥያቄና የኢትዮጵያ ኣንድነት ሁለት የማይነጣጠሉ የፖለቲካ መርሆዎች መሆናቸውን ለማሳየት እሞክራለሁኝ።

ኢትዮጵያ የብሔሮችና ብሔረሰቦች ኣገር ለመሆንዋ፡ የብሔር ጭቆናም እንደነበር የምያጠያይቅ ኣይደለም። ነገር ግን የብሔር ጥያቄው ከመጠን በላይ ተጋኖ ስለሚቀርብ፡ ባሁኑ ግዜ የታሪክ ሂደትና የመደብን ጥያቄ ኣስመልክቶ ትክክለኛ ትንታኔ ለማቅረብ የማይቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። በነገራችን ላይ የብሔርና የመደብ ጥያቄዎች ጣምራ ጥያቄዎች ከመሆናቸውም በላይ የኣንድን ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች እንጂ ሆድና ጀርባ እንዳልሆኑ መገንዘብ ይኖርብናል። ሌላ በቅጡ ማወቅ የሚኖርብን ነገር ቢኖር የብሔር ጭቆናና የመደብ ምዝበራ ኣድማሳዊ ባህርይ (universal applicability) ያላቸው እንጂ የኢትዮጵያ ብቸኛና ልዩ ታሪካዊ ተሞክሮ እንዳልሆኑ ነው። በተጨማሪ፡ እነኚ ክስተቶች የታሪክ ሂደት ነጸብራቆች እንጂ የወቅቱ የገዢ መደቦች ወይም የበላይነት ያላቸው የብሔር ኣባላት ሆን ብለው በንድፍ የሚተገብሩት ጉዳዮች ኣይደሉም። ባጭሩ፡ የብሔርና የመደብ ጥያቄዎች እጅግ የተወሳሰቡ ስለሆኑ በተለያዩ የታሪክ መድረኮች ላይ ኣንዳቸው ጎልቶ የሚታይበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ለምሳሌ፡ ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ሂደትና ኣወቃቀር (ባገር ግንባታ ላይ) ሓበሾች የበላይነትን ኣሳይተዋል፡ በ16ኛው ክፍለዘመን ደግሞ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች በሌሎች ኢትዮጵያውያን ላይ የበላይነት ነበራቸው፡ ስለሆነም ከቦሮና እስከ ትግራይ ከልዩ ልዩ ሕዝብ የተውጣጣ ቅይጥ ሕብረተሰብ ተፈጥረዋል ብንል ማጋነን ኣይሆንም። እንደገና፡ ምንም እንኳ ኣልባሹ ኃይማኖት ቢሆን፡ በ16ኛው ምእተ-ዓመት (ከ1520 እስከ 1540ዎቹ)፡ የበታችነት የነበራቸው እስላሞች በመሓመድ ግራኝ መሪነት የበላይነትን ኣግኝተው ነበር። በነበረው የጠመንጃ ብዛት ግራኝ ከሃረርና ሱማሌ ኣከባቢ የተውጣጡ ሰራዊቶች ይዞ እስከ ኣሸንጌ ደርሷል።

በዘመነ መሳፍንቱም ግዜ፡ ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ ባትነጣጠልም፡ ኣያሌና ኃያል መሳፍንት ተነሳስተው የኣንድነት ምልክት የሆነውን ንጉስ ኣቀርቁዘው ስለነበር፡ ያገርቷ ኣንድነትም ደፍርሶ ስለነበር፡ በብሔር የተደራጁ ክልላዊ መንግስታት ተቋቁሞው ነበር። ከኣጼ ቴዎድሮስ እስከ ኣሁን ደግሞ መደብና ኣንድነት (የብሔር ጥያቄ እንዳለ ሆኖ) የበላይነትን ኣሳይተዋል። በኣጼ ቴዎድሮስ የተጀመረውን የኢትዮጵያ ኣንድነት መሃልና ሰሜን ኢትዮጵያን ያካተተ ነበር፡ በኣጼ ዮሃንስ ስፋቱ እስከ ጅማ ይደርስና በንጉሰ-ነገስቱ ትእዛዝ ኣባ ጅፋር የጅማን ራስ-ገዝ ገዢ ሆኖ እንዲቀጥል ተወሰነ። በዛን ግዜ በንጉሰ-ነገስቱ ስር የራስ-ገዝ ኣስተዳደር የነበራቸው (ይኸም የፈደረሽን ጽንሰ-ሓሳብ ልንለው እንችላለን) የሸዋው ንጉስ ምንሊክ፡ የጎጃሙ ንጉስ ተክለኃይማኖትና የጅማው ኣባጅፋር ናቸው። ሆኖም ግን የውጭ ጠላቶች (ቱርኮች፡ ግብጾች፡ ጣልያኖች፡ ዱርቡሾች) ኢትዮጵያን ለመውረር ብዙ ግዜ መኩረው ስለነበር፡ በኣጼ ዮሃንስ ዘመነ መንግስት፡ ፋታም ስላልነበረ፡ ጠንካራ ማእካላዊ መንግስት ኣልነበረም ማለት ይቻላል። የጠንካራ ማእካላዊ መንግስት መልህቅ የተጣለው በኣጼ ምንሊክ ግዜ ነው። በዛን ግዜ ነው ኣሁን ደቡብ ኢትዮጵያ የምንለው (የኦሮሞ፡ የሲዳማ፡ የጉራጌ፡ ሃድያ፡ ከምባታ፡ ካፋ፡ ሃረር ወዘተ) በማእከላዊ መንግስት መስተዳደር ስር የወደቁት። ሓቁን ለመናገር ግን የደቡብ ሕዝብ በሰለማዊ መንገድ ኣይደለም የተቀላቀለው፡ በኃይልና በጦርነት ነበር የተያዘው። ኣጼ ምንሊክ ኣርሲን ብቻ ለመያዝ ስድስት ትላልቅ

ዘመቻዎች ኣካሂደ.ል። የጅማን ራስ-ገዝ ግን በኣጼ ዮሃንስ እንደተወሰነው እንዲቀጥል ኣጼ ምንሊክም ፈቅደዋል፥ ዳግማዊ ኣባጅፋርም እስከ 1930 ዓ.ም. ማለትም ኣጼ ኃይለስላሴ እስከነገሱበት ግዜ ድረስ መንግስትነቱን ይመራ ነበር።

ከዚሁ ከላይ ከጠቀስኳቸው ኣንዳንድ የታሪክ ሂደቶች ግን ማገናዘብ ያለብን ሦስት ነገሮች ኣሉ፥ 1) ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ማስፋት የተጀመረው ባጼ የሃንስ ወይም ባጼ ምንሊክ ብቻ ሳይሆን ቀደም ብሎም ሲደረግ የነበረ ነው። የዛሬ ሦስት ዓመት (December 2005) The Enigma of the Ethiopia-Somalia Relations and the Islamic Factor በሚል ጽሑፍ ሓበሾች ከኣዳሎች ጋር ባደረጉት ፍኩክር ኣቸናፊዎች ሆኖው በ1400 መጀመርያዎቹ ሃረርን ይቆጣጠሩ እንደነበር ኣመልክቻያለሁ፥ 2) ወደ ደቡብ ማስፋት ብቻ ሳይሆን ከደቡብም ወደ ሰሜን ማስፋፋት (ከፍ ብለን የጠቀስነውን የኦሮሞና የግራኝ እንቅስቃሴ) ከኢትዮጵያ ታሪክ ፍቀን የምናወጣው ነገር ኣይደለም፥ 3) በጦርነትና በኃይል ብቻ ሳይሆን በሰላማዊ መንገድ፥ በንግድና በጋብቻ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተወሳሰበ መንገድ እንደተቆራኘም መዘንጋት የለብንም። ለምሳሌ፥ ኣብዛኛው የሰባት ቤት ጉራጌ ሕዝብ የፈለሰው ከትግራይ፥ በተለይም ከጉራዕ (ኣሁን ኤርትራ ውስጥ) ለመሆኑ ኣፈ-ታሪክ ይናገራል፥ የኣገው ብሔረሰብ ኣባላት መሰረታቸው ላስታ ሆኖ ወደ ኲታ ገጠሙ ወደ ኣበርግሌ (ተምቤን) ብቻ ሳይሆን ወደ ኣገው ምድር (ጎጃም) እንዲሁም ወደ ከረን (ኤርትራ) ዘልቋል። የወሎ መልክዓ-ምድራዊ ኣቀማመጥ በርካታ የኢትዮጵያ ብሔሮችና ብሔረሰቦችን ያስተናገደ ነበር፥ ኣማራ፥ ኦሮሞ፥ አፋር፥ ትግራይ ለብዙ ሺ ዘመን ኣብሮ ኖሯል። ጎን ለጎን የሚኖሩ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ደግሞ ጦርነትና ደም መፋሰሱን ለማስወገድ በጋብቻ ይተሳሰሩ ነበር። የልዩ ልዩ ብሔሮች በጋብቻ መተሳሰር ጎልቶ የታየው ግን በኣጼ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት ነው። ማእከላዊ መንግስት ስለተጠናከረና በመጠኑም ቢሆን የቀላል ኢንዱስቱሪዎች መስፋፋት የታየበት ዘመን ስለነበር በርካታ የልዩ ልዩ ብሔር ተወላጆች ወደ መሃልና ደቡብ ኢትዮጵያ በመፍለስ ከሌሎች ብሔሮች ጋር ኣብሮው ኖሮዋል፥ በጋብቻም ተሳስሯል።

ይህ ከላይ የተነተንኩት የብሔሮችና ያንድነታቸው ምሳሌዎች ኣሁንም ቢሆን የኢትዮጵያ ብቸኛ ተመክሮ ሳይሆን ኣድማሳዊ ሓቅ የምያንጸባርቅ ክስተት ነው። የጥንት ብሔረ-መንግስታትና (ግብጽ፥ ኢትዮጵያ፥ ሮም፥ ግሪክ፥ ፐርዥያ፥ ቻይና ወዘተ) በ18ኛው መጨረሻና በ19ኛው መጀመርያ ክፍለዘመናት ባውሮጳ የተፈጠሩት ብሔረ መንግስታት፥ የያንዳንዱ ገጽታ የተለየ መልክ ያሳይ እንጂ ኣመጣጣቸው፥ ኣወቃቀራቸውና ኣከላላቸው ተመሳሳይ በሀርያትን ኣሳይቷል። ያሁኑ ዘበናይ ብሔረ መንግስታት (ከሶቭየት ሕብረት በስተቀረ) ከመላ ጎደል ጠንካራ ማእከላዊ መንግስት ነው ያቋቋሙት፥ ራስ-ገዝ ወይም ኣንጻራዊ ነጻ መስተዳደርን ይፍጠሩ እንጂ ኣንድነትን ነው ያጎለመሱት። ለኣንድነት (ስነልቦናዊና ቁሳቁሳዊ) ቅድምያ ባይሰጡት ኖሮ ደግሞ ካፒታሊዝምና ነጻ ገበያዎች ባለደጉም ነበር። በፈረካከሰ ኣገር የሃብት ክምችት ዕድገት ሊኖር ኣይችልም።

ለምሳሌ በሲዊዘርላንድ የኣራት የተለያዩ ብሔሮች ቋንቋዎች (ጣልያንኛ፥ ፈረንሳይኛ፥ ጀርመንኛ፥ ሮማኒሽ) ያገሪቷ የመስርያ ቋንቋዎች ሆነው ነው የምያገለግሉት፥ ግን ለጠንካራው ማእካላዊ መንግስት በይበልጥ የሚደላደልበት ሁኔታ ነው የፈጠሩለት። ኣመሪካ ውስጥ 50 የክልል መንግስታት (states) በፈደረሽን መዋቅር ነው የተቆራኙት፥ እያንዳንዱ ስተይት የራሱ ባንዴራ፥ የራሱ ፓርላማና የጎጥ መንግስት መስተዳደር ኣለው። ነገር ግን ማንኛውም ስተይት ከተባበሩት የኣመሪካን መንግስታት (United States of America) ተገንጥሎ መንግስት ማቋቋም ኣይፈቀድለትም። እንድያውም ኣመሪካ "የማትበታተን የተዋሃደች (indivisible whole) ኣገር ናት" ብሎ መንግስቱም ሕዝቡም ያምናል። ዘበናይቱ ቻይናም ተመሳሳይ ክስተት ኣሳይታለች፥ ማእካላዊ መንግስቱ ጠንካራ ሆኖ በኣዋሳኝ የሚገኙ ብሔረሰቦች ኣንጻራዊ የራስ-መስተዳደር መንግስት እንዲኖራቸው ተፈቅዶላቸዋል። የመገንጠል መብት ግን የላቸውም። የቻይና ተጨባጭ ሁኔታ ከሌሎች ኣገሮች ለየት የሚያደርገው ነገር ቢኖር ብዙሓኑ የሃን ተወላጆች ስለሆኑ ለኣንድነታቸው አመቺ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል ማለት ይቻላል።

የኢትዮጵያም ከነዚህ ከተጠቀሱት ኣገሮችና ተመሳሳይ ተመክሮ ያሳዩ ሕብረተሰቦች የሚለይ ኣይደለም። ግን ያገራችን ታሪክና የዓለም ዓቀፍ እውነታ በቅጡ ባላማወቅና ባለመገንዘብ ብዙ ስሕተቶች ተሰርቷል። ለምሳሌ በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ የብሔሮች የራስ ውሳኔና እስከ መገንጠል የሚል መርሆና መፈክር ማእከላዊ ቦታ ይዘው ነበር። ባንድ በኩል የተማሪው ንቅናቄ ፍትሓዊ ጥያቄዎችን ይዞ ነበር የቀረበው -- የብሔር ብቻ ሳይሆን "የሴቶች እኩልነት"፡ "መሬት ላራሹ" "ድህነት ወንጀል ኣይደለም" ወዘተ የሚሉ መፈክሮችም በማንገብ ተነስቶ ነበር። በሌላ በኩል ግን፡ የብሔር ጥያቄን ኣስመልክቶ፡ ኣጉል ትንታኔ ብቻ ሳይሆን የሦስቱ ስላሴ (ይቅሬታ ምእመናን!) ማለትም የማርክስ፡ ለኒንና ስታሊን ርእዮተ ዓለም በጭፍን በመቀበል ስላስተጋባ፡ ኣሁን ወደ ኋላ መለስ ብለን ስናየው የጨቅላ ፖለቲካ እንቅስቃሴ ነበር የተካሄደው ማለት ይቻላል። በርግጥ የብሔሮች መብት መጠበቅ ፍትሓዊ ብቻ ሳይሆን ኣስፈላጊም ነው፡ ለኣንድነታችንም ጠንካራ መሰረት ይጥላል። መገንጠል የሚባለው ዘይቤ ግን እንኳንስ ለድሃና ለታዳጊ ለሆነችው ኢትዮጵያ ኣገራችን፡ መጥቃ ለነበረችው ለሶቭየት ሕብረት እንኳ ኣልበጀችም።

ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያን ሕዝብ ኣንድነት ለማጠናከርና የኢትዮጵያን ልዑላዊነት በቀና መንፈስና በንጹህ ልቦና መጠበቅ ከፈለጉ ከመቸውም ግዜ ንቃተኅሊናቸውን ማጎልመስ ኣለባቸው። በተጠንቀቅ መቆም ኣለባቸው። በትምክህተኞችና በጠባብ ብሔርተኞች የሚታዩትን ኣዝማምያና ኣክራሪነትን ኣጥብቀው መታገል ኣለባቸው። ኣንድነትን ለመጠበቅ ደግሞ ኣንድነት ያስፈልጋል! ኢትዮጵያውያን ከመቸውም ግዜ እንደ ኣንድ ወጥ ኅብር ሆኖው መንቀሳቀስ ኣለባቸው።

የኣንድነት ኣፈቀላጤዎች መልተዋል፡ የሕዝቡን ኅብረት የሚጠብቁ ግን እምብዛም ኣይደሉም። በኣፍ ኢትዮጵያዊ በግብር ግን የጎጥ ፖለቲካ ኣርበኛ መሆን እጅግ በጣም ኣደገኛ ነው። ኣንድነታችን መጠበቅ ከፈለግን የሰላም፡ የፍቅርና የእኩልነት የጋራ ቤት የሆነችውን ኅብረ-ብሔር ኢትዮጵያን (በስነልቦናም በግብርም) ማነጽ ይኖርብናል። የእውነትና ዘሌቄታ ያለው ኣንድነት መመስረት የምንችለው ደግሞ በማኰረፍ፡ በመናናቅና በጥላቻ ፖለቲካ ተዘፍቀን ሳይሆን በመከባበር፡ በመተማመንና በመቀራረብ ኣንድነታችንን ስናጠናክር ብቻ ነው።

ኣንዳንድ ግዜ እርስ በራሳችን የምንናቆረው ካለማወቅ የተነሳ ሊሆን ይችላል። ብዙ ወገኖቻችን ከፍ ብሎ ለተጠቀሰው የኢትዮጵያ ታሪካዊ ኣመጣጥና ኣወቃቀር ወይ ከነጭራሹ ኣያውቁትም ወይ ደግሞ ደብዘዝ ባለ መንገድ ነው የሚገነዘቡት። ስለሆነም የኣማራን ሕዝብ እንደ ጠላት ኣድርጎ ማቅረብና መፍትሔው ደግሞ መገንጠልና የራስ መንግስት ማቋቋም ነው የሚሉ ይሆናሉ። ይኸንን በሚመለከት ቀደም ብየ የጻፍኩትን "ለኢትዮጵያ የሚበጅ የፖለቲካ ስትራተጂ መቀየስ የሁላችን ታሪካዊ ኃላፊነት ነው" (We Have Historical Obligation in Strategizing for the Future of Ethiopian Politics; Please go to the following link: http://www.africanidea.org/doc5.pdf ) በሚል ርእስ በግልጽ ኣስፍሬዋለሁ። ለምሳሌ ያህል፡ ከጠቀስኳቸው ኣንዳንድ ፍሬነገሮች የሚከተሉት ናቸው፦ "ኣሁን ኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጠረው የፖለቲካ ቀውስና ያስከተለው የምልኣተ ሕዝቡ ስጋት፡ ብሎም ዝቅተኛ ንቃት ያላቸው ዜጎች መደናበር በይበልጥ ጽልመተ-ዓለም ኢትዮጵያን ከፍተኛ ችግር ላይ ጥሏታል ማለት ይቻላል። እንኳንስ ዘንቦብሽ እንድያውም ጤዛ ነሽ እንዲሉ በነበረን ችግር ላይ ውዥንብር ሲጨመርበት የባሰ ማጥና ኣዘቅት ውስጥ ነው የምንገባው። የችግሩ መንስኤ እኛው ነን፡ የምንፈታውም እኛው ነን።"

ኣንዳንድ ኃላቀር ትምክህተኞች ግን የጽሑፌን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ከመተንተን ይልቅ "የጸጸት ጽሑፍ ነው" በማላት ኣትቷል። እኔ የምጸጸጥበት ጉዳይ የለኝም፡ ምንግዜም የኢትዮጵያን ኣንድነት ለማራማድ ነው የታገልኩት። የብሔሮች መብትም የምደግፈው ከኢትዮጵያ ኣንድነት በማጣመር ብቻ ነው። ኣሁንም ቢሆን በግል ደረጃ ኢትዮጵያን ከምያስቀድሙ ኃይሎች ጎን ነው የምሰለፈው። ኣንዳንድ ግዜ ደግሞ ካለማወቅ ወይም ከየዋህነት ሳይሆን ሆን ተብሎ የኢትዮጵያን ኣንድነት ለማደፍረስ ሌት ተቀን የሚጥሩ ሴረኞች ኣሉ። የነዚህ ተግባር በተለያየ መልክ ሊንጸባረቅ ይችላል። ኣንዳንድ ምሁር ነኝ ባይ "ኢትዮጵያ ከትግራይ መገንጠል ኣለባት" (ርእሱ

ራሱ መሳቅያና መሳለቅያ ነው) የሚል ሲሆን ሌላው ደግሞ፣ ወደ በታኝ ወጥመድ መግባቱን ሳይገነዘብ፣ ማሸቲ ይዞ “ትግሬ ገዳይ” ብሎ የሚጨህ የዋህ ስብስብ ነው።

ነገር ግን፣ በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ የበሰለና ሰፋ ያለ ኣመለካከት ስላለ፣ የኢትዮጵያም ሕዝብ በጨዋነቱ የታወቀ፣ እርስ በራሱ የማይፈላለግ፣ ግን ኣብሮ መኖር የሚፈልግ ስለሆነ፣ መጭው የኢትዮጵያ ዕድል ብሩህ እንደሆነ ይታየኛል። ግን ምን ይታወቃል፣ ሴረኞች በሕቡእ ስለሚንቀሳቀሱ፣ ሆን ብለውም ሕዝቡን የሚያጋጭ ጠብ መጫር ስለሚችሉ በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተንጠልጥሎ እንዳይሆን በተጠንቀቅ መንቀሳቀስ ይኖርብናል።

መልካም ዕድል ለኢትዮጵያ!